ይታዩኛል፡ የኢሕ አ ፓ ሰማዕታት፤ ድምጻቸውም ይሰማኛል

ይታዩኛል፡ የእምዬ የኢሓአፓ ሰማዕታት

የእምዬ ኢትዮጵያ ሰማዕታት

እኒያ የለውጥ ሐዋሪያት

በደል ፣ ጭቆናና፣ ብዝበዛን እንዲወገድ

ለባህልና ለቋንቋ እኩልነት እንዲሰፍን

ፍትህ ፣ የሕግ፣ የበላይነትና ዲምክራሲ ለማስፈን

ውድ ሕይውታቸውን የሰጡት

ትግሬ፡አማራነህ

ኦሮሞ፡ ጉራጌነህ

ከባታ፡ ዶርዜነህ

ሱማሌ፡ ሲዳማነህ

እስላም፡ ክርስቲያነህ

ሃብታም፡ ደሃነህ ሳይሉ

በጎሰኝነትና በሃይማኖተኝነት በሽታ ሳይመረዙ ፤ ሳይበከሉ

በአንድነት የጠጡ፡ በአንድነት የበሉ

ለአንድ ሕዝብ ለአንድ ኢትዮጵያ

በአንድነት የታገሉ

በአገርና በሕዝብ ፍቅር የተቃጠሉ

ይታዩኛል ። የእምዬ ኢ ሕ አ ፓ እንጾች

የእምዬ ኢ ሕ አ ፓ ኩትኩቶች

የእምዬ ኢትዮጵያ ጀግኖዎች

ሞት አይፈሬዎች። ቆራጦች

ከመድፍ ፣ከመትረየስ፣ ከታንክ። ተፋላሚዎች

ይታዩኛል። እነዚያ ዘለግላጋዎች።

እነዚያ ሎጋዎች

ቀያይዎች የቀይ ዳማዎች

አልማዝ መሳይ ጡቋቁሮች

ዓሣ መሣይ ጠያይሞች።ባለውበቶች

ተረሽነው በጸረ ሕዝብ ካድሬዎች

ተመትረው በአገር በቀል ፋሽስቶች

ይታዩኛል። በየመናህሬው ወድቀው

በየጉራንጉሩ፣ በየደጃፉ ተዘርረው

እንደቄራ በሬ ታርደው

እንደጎርፍ ሲፈስ ።አፈር ሲጠርግ ደማቸው

ይታዩኛል እነዚያ፡ የጭቁን አርሶ አደር

የጭቁን ወታደር

የጭቁን ላብ አደር ልጆዎች

አካለ ኮስማኖች

መንፈሰ ጽኑዎች

ልበ ደንዳኖች

ለዓላማ ፡ለቃል ኪዳን ሟቾች

ይታዩኛል፡ በየአደባባዩ ተደፍተው

በደም ተለውሰው

አንገታቸው በጥይት ተቀንጥሶ

የራስ ቅላቸው ን ተቦድሶ

ዓይኖቻቸውን ተነቁሮ

ክንዶዎቻቸው ን ተሰባብሮ

ይታየኛል ፡ ሥቃያቸው ከየእሥር ቤቱ

ለሊቱ ሙሉ ሲቀጠቀጡ ሲመቱ

ጥፍሮቻቸው በጉጠት ሲነቀል

ጠርሙስ በልቶቻችው ላይ ሲንጠለጠል

ሲቀረቀር ኳስ በአፋቸው

እንደ ልኳንዳ ሥጋ ተሰቅለው

እንደ ፍየል ቆዳ ተውጥረው

በቆዳ ጅራፍ ሲገለሽጧቸው

በኮረንቲ ገመድ ሲገርፏቸው

ይሰማኛል፥ይሰማኛል ድምጻቸው

አንዳችም ሚስጥር አለማውጣታቸው

ፍንከች ንቅንቅ አለማለታቸው

በቃል ኪዳን መጽናታቸው

ፋሽስት ደርግዎች ይወድማሉ !

ፀረ ሕዝብ የደርግ ካድሬዎች ይወድማሉ !

ኢ ሕ አ ፓ እና ሰፊው የኢትየጵያ ሕዝብ ያሸንፋሉ !

እያሉ መፈክር ሲያሽጎደጉዱ

የፀረ ሕዝቦዎች አሞት ሲያሽመደምዱ

ይታዩኛል ጓዶቼን ፥

በውድቀተ ለሊት ተቀስቅሰው

እጆቻቸውን የኋሊት ተጠፍረው

በጂፕ፣ በማክ፣ በላንድሮበር ተጭነው

ሲወስዷቸው ሊፈጅዋቸው

የጅምላ ግዲያ ሊፈጽሙባቸው

ይሰማኛል ደምጻቸው ፥

ፍጹም ነው እምነቴ

የትግል ነው ሕይወቴ

እያሉ ሲዘምሩ

የገዳዮቻቸውን መንፈ ሲያስጨንቁ፡ ሲያሸብሩ

ሞት ማን ይፈራል!

ታጋይ ይሞታል

እንጂ አይሞትም ትግል!

ለዓላማ መሞት

ለመተከል መሞት

የክብር ሞት ነው ! ማለታቸው

ጮክ ብለው መፎከራቸው

ይታዩኛል፥ በክላሽኮቭ፡ በመትረስ ተረፍርፈው

በየጫካው ተጥለው

በየወንዙ ዳር ተጋድመው

በየዋሻው ተከማችተው

የአውሬ፡ የአሞራ ፈንጠዚያ ሁነው

ተከምረው በጅምላ መቃብር

ሲጭኑባቸው አፈር በግሬደር

ከማውቃችሁ ላንሣችሁ ጥቂቶቻችሁ

ሁሌ ስለሚታየኝ ገጽታችሁ

ሁሌ ስለሚታየኝ ፍጹም ሕዝባዊነታችሁ

ሁሌ ስለሚታየኝ ሰከነታችሁ፤ ብስለታችሁ

ሁሌ ስለሚታየኝ አርበኝነታችሁ

እስቲ ለናሙና ላንሳቹሁ ፥

ወደልዓብ ደንቡ ፣ ግዛው ናማጋ ፣ ተድላ ወርቁ ፣ ተከተለው ተፈራ፣ ጀማል ፣ ሰለሞን፣ ሞገስ፣ ናሥር፣ አህመድ ፣ ታዬ፣ጥላሁን

ተቸገርኩኝ ፡ማንን አንስቼ ማንን ለመተው

ሁላችሁም ጓዶቼ በመሆናቸው

ሁላችሁም የእኔ በመሆናቸው

ሁላችሁም በአንድ ዓይን ስለማያቸው

እሪ በል የአገሬ ምድር

እረ በል የአገሬ አድባር

እሪ በል የአገሬ ሰማይ፤ የአገሬ ጠፈር

እሪ በሉ የአገሬ መንፈሳት

እሪ በሉ የአገሬ ወንዛት

እሪ በሉ የአገሬ ገዳማት

እሪ በሉ የአገሬ ታቦታት

እሪ በሉ የአገሬ መስጊዳት

እሪ ! እሪ !! በሉ በደርግ ሥራዓት

ለተፈጁት ፣ ለታረዱት

ለዕሩብ ምሊዮን ሰማዕታት

የኢሕ አፓ ሰማዕታት ገድልና ስም ሕያው ሆኖ ይኖራል!

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ይወድማሉ!

እናት ኢትዮጵያ ለዘላዓም ትኑር!

ታጠቅ ሚንጃ